የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 33
ADDIS ABABA - 28th June, 2001


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፭/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
ለርቀት ትምህርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ ፭፻፴፭


## አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፭/፲፱፻፺፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለርቀት ትምህርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፫ ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፩ ቀን ፪ሺ ፩ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለርቀት ትምህርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፭/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## CONTENTS


Proclamation No. 245/2001
International Development Association Credit Agreement for Financing the Distance Learning Project Ratification Proclamation ........... Page 1535


*PROCLAMATION NO. 245/2001*

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION*

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 3,900,000 (three million nine hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Distance Learning Project was signed in Washington D.C. on the 1st day of May, 2001;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 28th day of June, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing the Distance Learning Project Ratification Proclamation No. 245/2001."

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ ልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፩ ቀን ፪ሺ፩ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፭፻፩ኢ.ቲ. የብድር ስምምነት ነው ።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ፕሬዚዳንት



2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No. 3501ET signed in Washington D.C. on the 1st day of May, 2001, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 3,900,000 (three million nine hundred thousand Special Drawing rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of June, 2001.

Done at Addis Ababa, this 28th day of June, 2001.

NEGASO GIDADA(DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE